ቢኮሎስ ኑር አካዳሚ

ለ8ተኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲረዳ ሆኖ የተዘጋጀ የሥነ-ዜጋና ሥነ-ምግባር ት/ት ሳምንታዊ ማስታወሻ

ምዕራፍ 9- የቁጠባ ባህል

9.1 የቁጠባ ባህል መዳበር አስፈላጊነት

- **ቁጠባ** ማለት ከሚገኝ ገቢ ላይ በአግባቡ ለሚያስልግ ወጪ ተጠቅሞ የተወሰነውን ለወደፊት ጠቃሜታእንዲሆን ማስቀመጥ ማለት ነው፡፡
- *ቁጠባ አስፈላጊካልሆኑ ወጪዎች መታቀብንያመለክታል፡፡*

ቁጠባ ጊዜን ፣ ጉልበትን እውቀትን በአግባቡ ተጠቅሞ ጠንክሮ ለመስራት በተገኘ ገቢ ለወደፊት የሚሆን ንብረት በገንዘብ ወይም በአይንት ማስቀመጥ ማለት ነው፡፡

እያንዳንዱ ሰው በእለትም ሆነ በተወሰነ ግዜ የሚያገኘውን ገቢ ለኑሮው አብቃቅቶ ለወደፊት ኑሮው የሚውል ገንዘብ ማጠራቀም አለበት፡፡

- *ቁጠባ በዜግነት የሚጠበቁ ግዴታዎችን ለመወት ይጠቅማል፡፡ (**ለምሳሌ** ግበር መክፈል) መንግስት ትምህርትቤቶችን የሚያስፋፋው ከህዝብ በተሰበሰበ መዋጮዎች ነው፡፡*

ቁጠባ በአግባቡ ለመቆጠብ የቁጠባዘዴዎችን መከተል ያስፈልጋል፡፡

- **የቁጠባ ዘዴዎች የሚባሉት ፡-**

  ፩ አላስፈላጊ ወጪዎችን መቀነስ

  ፪ ራስን እና ቤተሰብን በእቅድ ማስተዳደር

- **የቁጠባ አይነቶች የሚባሉት**

  ፩ በአይነት የሚደረግ ቁጠባ (እንሰሳት ማርባት፣ አፅዋት መትከል)
  ፪ የገንዘብ ቁጠባ
  ፫ የግዜ ቁጠባ ናቸው፡፡

- **የቁጠባ አስፈላጊነት**

  - ለሚጠበቁ አጋጣሚዎች ይውላል
  - ቋሚ ንብረት ለማፍራት
  - ለማይጠበቁ አጋጣሚዎች ይውላል
  - እራስን ለመቻል
  - ኑሮን ለመምራት
  - ለሀገር እድገት.

የቁጠባ ባህል መዳበር የሚጠቅመው ለግል ብልጽግና ብቻ አይደለም፡፡ የዳበረ የቁጠባ ባህል ያላቸው ሰዎች ለሀገር እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡



ሣምንታዊ መልመጃ

የምዕራፍ 9ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ትዕዛዝ ፡-1,2,3

በ መር/ት እንግዳሸት አሊ

ሚያዝያ 27/2012 ዓ.ም